# ያለ በቂ መረጃ መኪናን ማከራየት ለተጠያቂነት ይዳርጋል

በእስክንድር መርሐጽድቅ

*የመኪና አከራዮች መኪናቸውን ለማን እና ለምን አገልግሎት እንደሚያከራዩ ሳያረጋግጡ ማከራየት እንደሌለባቸውና በዚህም በሚደርስ ጉዳት ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ ተጠቆመ፡፡*

*በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ መቆጣጠሪያ ጣቢያ አስተባባሪ አቶ ተክሊል ዋልጋ እንደገለፁት አንዳንድ ግለሰቦች የተከራዩዋቸውን መኪኖች ለህገወጥ ተግባር እየተጠቀሙበት ነው፡፡ በዚህም ቢያንስ በአንድ ወር ውስጥ አምስት በኪራይ የተያዙ መኪኖች የኮንትሮባንድ እቃ ይዘው መገኘታቸው ለዚህ ማስረጃ ነው ብለዋል፡፡*

*በመሆኑም አከራዮች የተከራዮችን ማንነት ከመታወቂያቸው ሙሉ ማስረጃ መያዝ እንዳለባቸውና የተከራዩትም ለምን አገልግሎት እንደሆነና የት እንደሚወስዷቸው ክትትል ማድረግ እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡*

*የኮንትሮባንድስ ነጋዴ የግል ንብረቱ በሆነ ተሽከርካሪ የኮንትሮባንድ እቃ ይዞ ከተገኘ ተሽከርካሪው እንደሚወረስ ስለሚያውቅ ወደ መከራየት እንደሚሄዱ አመልክተዋል፡፡ ኮንትሮባንዲስቶቹ በተከራዩዋቸው ተሽከርካሪዎች ጭነው ከተገኙ ደግሞ እንደተጫነው የኮንትሮባንድ እቃ የቀረጥ ታክስ መጠን የተሽከርካሪው ባለንብረትም የገንዘብ ቅጣት እንደሚጣልበት አስታውቀዋል፡፡ ይህ ቅጣት የሚጣለው አከራዩ ከኮንትሮባንድ ከሚገኘው የጥቅም ተካፋይ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ መሆኑን ገልፀዋል፡፡*

*ከእነዚህ አይነቶቹ ድርጊቶች መካከል ግንቦት 1/2002 ዓ.ም. ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን በአቃቂ ቃሊቲ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የተከሰተው አንድ ምሣሌ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በእለቱ 20 ዓይነት የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ተጭኖበት የተገኘው የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-10080 ኢ.አ. የቤት መኪና አሽከርካሪው በኪራይ ይዞት የነበረ እንደሆነ አስታውሰዋል፡፡*

*ባለንብረቱ የኮንትሮባንድ እቃውን የጫነው ናዝሬት ላይ ሲሆን ለጫነበትም ለአሽከርካሪው 300 ብር ሊከፍለው ተዋውሎ እንደነበር መናገሩን፣ አሽከርካሪው ደግሞ መኪናውን ተከራይቶ እንደያዘውና የጫነው እቃ ምን እንደሆነ እንደማያውቅ መግለፁን ጠቁመዋል፡፡*

*በተመሣሣይም በኪራይ በተያዘና የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ-2 52349 አ.አ. የሆነ የቤት መኪና ግንቦት 17/2002 ዓ.ም. ከቀኑ 9 ሰዓት ተኩል ላይ በርካታ የመኪና መለዋወጫና ዕቃዎችን ጭኖ ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ ሊገባ ሲል በዚሁ መቆጣጠሪያ ጣቢያ መያዙን አመልክተዋል።*

*የመኪናው አሽከርካሪ መኪናውን ለመዝናኛ አገልግሎት በቀን 500 ብር ሂሣብ ተከራይቶ እንደነበረ አመልክተዋል። አብረውት የተያዙት ሶስት ግለሰቦች ደግሞ አሽከርካሪው ለጫነላቸው ዕቃ 500 ብር ሊከፍሉት ተዋውለው እንደነበር ከሰጡት ቃል ለመረዳት መቻሉን ገልፀዋል።*

*በዚሁ ተሽከርካሪ ከ10 ቀናት በፊት ማንነታቸው ለጊዜው ያልተወቀ ሰዎች በጣቢያው ፈታሾች መኪናውን ለፍተሻ እንዲያቆሙ ሲጠየቁ ኬላ ጥሰው ማምለጣቸውን አስታውሰዋል።*

*በአምስት ሻንጣችና በአምስት ማዳበሪያዎች ታስረው ከሁለቱም መኪኖች ላይ የተያዙት የመለዋወጫ እቃዎች ግምት ዋጋቸው ቀረጥና ታክሱን ጨምሮ ብር 695 ሺ 844 እንደሆነ ገልፀው ተከራዮችም ሆኑ የመኪና ባለንብረቶች የሚጭኑትን እቃ ምንነት ሳያውቁ መጫን እንደሌለባቸው አሳስበዋል።*